ሰሜን ሪጅን ኢትዮ ቴሌኮም ተለይተው የተቀመጡ የተለያዩ ያገለገሉ እቃዎች በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መሸጥ ይፈልጋል።

- የተለቀቀበት ቀን: ሰሉስ ሚያዝያ 20, 2018 (ከ 7 ወር)
- መዝግያ ቀን: ጉንበት 6, 2018 8:00 ጥዋት (ተዘጋ)
- የጨረታ ማስከበርያ ዋጋ:በየ ሎቱ ይለያያል
- ቦታ:መቐለ
- የጨረታ ደኩመንት ዋጋ:100
- ጨረታ ሚከፈትበት ቀንና ሰዓት: ጉንበት 6, 2018 8:15 ጥዋት
- ምድብ: ካልኦት ዝሸወጡ/ ዘገልገሉ ኣቅሑት መሸጣ/

ጨረታ ቁጥር SC&C/04/2018

ሚያዚያ 20 ቀን 2018 ዓ.ም

ሰሜን ሪጅን ኢትዮ ቴሌኮም ተለይተው የተቀመጡ የተለያዩ ያገለገሉ እቃዎች በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መሸጥ ይፈልጋል።

1. ተጨራቾች በቅድሚያ አዉቀዉ ማቅረብ ያለባቸዉ

1. ዝርዝር መግለጫ የያዘውን የጨረታ ሰነድ ከ ሚያዚያ 20 ቀን 2018 ዓ.ም እስከ ግንቦት 06 ቀን 2018 ዓ.ም ዘወትር በሥራ ሰዓት ከሰኞ እስከ ዓርብ መቐለ ዋና ቢሮ ቁጥር 301 በመምጣት የማይመለስ ብር 100.00 (ብር አንድ መቶ) በመክፈል መውሰድ ይችላሉ።

2. ተጫራቾች የዘመኑን ግብር የከፈሉና የ2018 ዓ.ም ታደሰ ንግድ ፍቃድ ማቅረብ ይኖርባቸዋል::

3. ተጫራቾች በጨረታው ለመሳተፍ የጨረታ ዋስትና ማስከበሪያ በአንድ ጨረታ ከብረታብረት ውጪ ላሉት ለመሳተፍ ብር 30,000.00 (ሰላሳ ሺ ብር) ለብረታብረት ጨረታ ለመሳተፍ ብር 50,000 (ሃምሳ ሺ) ሲፒኦ (CPO) አጠቃላይ ለብረታብረት እና ለሌሎች ለመሳተፍ 80,000 (ሰማንያ ሺህ ብር) ማስያዝ ይኖርባቸዋል።

4. የጨረታ ማስከበሪያው ከታወቀ ባንክ ተረጋግጦ በሚቀርብ ሲፒኦ (CPO) ብቻ ሊሆን ይገባል::

5. ተጫራቾች ዕቃዎችን የሚገዙበትን ዋጋ በጨረታ ሰነዱ ላይ በሚቀመጠው ዋጋ ማቅረቢያ ቅጽ/ፎርም በተቀመጠው መሰረት ያገለገሉ የተለያዩ እቃዎች ዋጋ ከቫት በፊት ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

6. ጨረታው ከመዘጋቱ በፊት የጨረታ ሰነዱን በመግዛት ዋጋ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

7. አሸናፊ የሚሆነዉ ተጫራች ካሸነፈዉ ዋጋ በተጨማሪ ቫት ጨምሮ ገቢ ካደረገ በኋላ በአስር /10/ የስራ ቀናት ዉስጥ ለጨረታ ተለይተዉ የተዘጋጁ ያገለገሉ የተለያዩ እቃዎች ብቻ ማንሳት አለባቸዉ:: ሆኖም ግን በጊዜ ገደቡ ካላነሱ ለጨረታ ማስከበሪያ ያስያዙት ሲፒኣ /CPO/ _ ለሪጅኑ ገቢ ተደርጎ ሪጅኑ የራሱን አማራጭ ይወስዳል ::

8. አሸናፊ ተጫራች/ ተጫራቾች በተቀመጠዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ በራሳቸዉ ወጪ ዕቃዎችን ማንሳት ይኖርባቸዋል ::

9. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን የገዙበትን ደረሰኝ በመያዝ ዕቃዎቹ በሚገኙበት ሓሚዳይ በሚገኘው እቃ ግምጃ ቤት እና አዋሽ የእህል መጋዘን አጠገብ በሚገኘዉ ኢትዮ ቴሌኮም ጋራዥ ግቢ ዉስጥ፣ በዋናው መ/ቤት አደራሽ እንዲሁም በመሰቦ ኢትዮቴሌኮም ግቢ እየቀረቡ ማየት ይችላሉ።

10. ተጨራቾች አስፈላጊዉን የመወዳደሪያ ሰነዶችን በፖስታ አሽገዉ ማስገባት ያለባቸዉ ከ ሚያዚያ 20 ቀን 2018 ዓ.ም እስከ ግንቦት 06 ቀን 2018 ዓ.ም ከቀኑ 08፡00 ሰዓት ድረስ ብቻ ይሆናል። ከነዚህ ቀናትና ሰዓታት በኋላ የሚቀርብ የጨረታ ሰነድ ተቀባይነት የለውም።

11. ጨረታው ተጫራቶች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በኢትዮ ቴሌኮም ዋናው መ/ቤት ቢሮ ቁጥር 301 ግንቦት 06 ቀን 2018 ዓ.ም ከቀኑ 8:15 ሰዓት ይከፈታል።

12. ተጫራቾች ጨረታው ከተከፈተ በኋላ ያቀረቡትን ዋጋ ለመለወጥ ወይም ለማሻሻል አይችሉም።

13. የጨረታው ውጤት ሳይታወቅ ውድድሩን ማቋረጥ የሚፈልግ ተጫራች ያስያዘው የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ለመስሪያ ቤቱ ገቢ ይደረጋል።

14. የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ያላቀረበ ተጫራች ጨረታው በሚከፈትበት ወቅት ወዲያውኑ ከጨረታው ይሰረዛል።

15. ተጫራቾች ላሸነፉት ንብረት አጠቃላይ ዋጋ ቫትን ጨምሮ በኢትዮ ቴሌኮም ንግድ ባንክ አካውንት ገቢ በማድረግ ማንሳት ይጠበቅበታል።

16. ተጫራቾች የማስመዘኛና የማስጫኛ እንዲሁም የሰራተኛ ወጪ በተጫራቹ የሚሸፈን መሆኑ በመገንዘብ ዋጋውን ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል።

17. ኢትዮ ቴሌኮም የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

18. ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ መጫረት ይቻላል።

ምልክታ እና ቅጂው:: 2013 - 2026 Made with love in Mekelle